በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS
የፕሬስ መግለጫ
PRESS RELEASE

**ኢትዮጵያና ቻይና ወዳጅነታቸውን ለማጠናከር ተስማሙ፡፡**

የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ ከቻይና አቻቸው ዋንግዩ ጋር በሁለትዮሽ እና በባለብዙ ወገን ጉዳዮች ላይ ተወያዩ፡፡

ዶ/ር ወርቅነህ በዚሁ ወቅት የኢትዮጵያና የቻይና ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበተ መምጣቱን ገልፀው ይህን ወዳጅነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የሚያስችል ዕድል መፈጠሩንም ተናግረዋል፡፡

ቻይና ኢትዮጵያን በመጠነ ሰፊ ስትራቴጂካዊ አጋርነት ደረጃ ማስቀመጥዋ እና ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ ቤጂንግ በተካሄደው “የአንድ መቀነት አንድ መንገድ” ስብሰባ ከአፍሪካ አገራት ብቸኛ ተናጋሪ ሆነው መጋበዛቸው ለዚህ ማሳያ መሆኑን ሚኒስትሩ ተናግረዋል፡፡

የቻይናው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኢትዮጵያ በቤጅንጉ ስብሰባ ላይ በጠቅላይ ሚኒስትር ደረጃ በመሳተፍ አጋርነቷን ማሳየቷን ጠቅሰው አገራቸው የኢትዮጵያውያን የኢንድስትሪ ፣ የመሰረት ልማት እና የአቅም ግንባታ እንቅስቃሴ ለመደገፍ ቁርጠኛ መሆኗን ተናግረዋል፡፡

ቻይና ከአፍሪካ ጋር በምታደርገው ትብብር ኢትዮጵያ የግኑኝነት መስመር ማዕከል ናት ያሉት የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሁለቱ አገሮች በፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት በአፍሪካ ቀንድ ሰላም ጉዳዮች ላይ ተቀናጅተው እንዲንቀሳቀሱ ፍላጎታቸውን ገልጸዋል፡፡

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

**ቃል አቀባይ ጽ/ቤት**

**ሰኔ 14 ቀን 2009 ዓ.ም.**